
DEPARTMENT OF ECOLOGY State of Washington

# Boathouse Inc Renton Skyway የጽዳት አካባቢ




Boathouse Inc Renton Skyway የጽዳት አካባቢ

## ስተያየቶች ገቢ ተደርጓል

**ጁላይ 18 – ኦገስት 16, 2022**

## አስተያየቶችን መስመር ላይ/ኦንላይን የሚከተለው ላይ

**በመሄድ ገቢ አድርግ፡**
https://bit.ly/Ecology-Boathouse-Comments

**ወይ በፖስታ ለ፡**
Sandra Matthews, Site Manager
WA Department of Ecology
PO Box 330316
Shoreline, WA 98133-9716
425-223-1999
sandra.matthews@ecy.wa.gov

## የሰነድ ግምገማ መገኛ ቦታዎች

https://bit.ly/Ecology-Boathouse

Skyway Library
12601 76th Ave S
Seattle, WA 98178
206-772-5541

**Department of Ecology**
**Northwest Regional Office**
15700 Dayton Ave N
Shoreline, WA 98133
*እባክዎ ቀጠሮ ለመያዝ ወደ እሚከተለው ይደውሉ፡* 206-594-0000

## የጽዳት ቦታ መረጃ

Facility Site ID: 56652786
Site Cleanup ID: 567

## የጽዳት ሂደቱ ወደ ፊት በመሄድ ላይ

Department of Ecology (Ecology) (የኢኮሎጂ የስራ ክፍል) በ Skyway የመኖሪያ መንደር በ Boathouse Inc Renton Skyway አካባቢ በ GardnerGlobal, Inc (GG) የሚካሄደውን የጽዳት ስራ በበላይነት በመምራት ላይ ይገኛል። Ecology በአዲሱ Affordable Housing Cleanup Grant Program (በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የመኖሪያ ቤት ጽዳት የገንዘብ ድጋፍ መርሃ ግብር) በኩል ለዚህ የጽዳት ስራ የሚውል የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። የዚህ መርሃ ግብር ዓላማ "ጽዳት የሚካሄድባቸው ቦታዎች በሚገባ እንዲጸዱ እና በሂደቱም የማህበረሰብ ተሳትፎ እንዲያስፋፉ እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የመኖሪያ ቤቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው።"

በሚከተሉት ሰነዶች ላይ የእርስዎን አስተያየት እንፈልጋለን፡

**የገዢ የፍቃድ አዋጅ (Prospective Purchaser Consent Decree, PPCD):** ገዢ ጽዳት በሚካሄድበት ቦታ ላይ ጽዳት እንዲያካሂድ ትዕዛዝ የሚሰጥ እና ገዢው ክፍያ እንዲፈጸምለት የሚያደርግ ህጋዊ ስምምነት ነው።

**የህዝባዊ ተሳትፎ መርሃ ግብር:** ሰነዱ ሰዎች በጽዳት ሂደቱ ላይ እንዴት ተሳታፊ መሆን እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው።

## የኦንላይን ህዝባዊ ውይይት

የህዝቡን ጤና እና ደህንነት ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻል ዘንድ፣ Ecology ተጨማሪ መረጃ ለማጋራት እና ጥያቄዎችን ለመመለስ የኦንላይን ህዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል። **ምዝገባ ያስፈልጋል።**

**ረቡዕ, ኦገስት 3, 2022**
6:30 – 7:00 p.m. ገለጻ
7:00 – 7:30 p.m. የጥያቄ እና መልስ መርሃ ግብር

የምዝገባ እና የአባልነት ዝርዝሮችን ለማግኘትhttp://bit.ly/Ecology-Boathouse ን ይጎብኙ።

## ዳራ

Boathouse Inc. Renton Skyway site (site) በ Skyway, king county, Washington የሚገኝ በፊት የችርቻሮ እና የ ደረቅ ጽዳት አገልግሎት ሰጪ የነበረ ህጋዊ በሆነ መልኩ ያልተቋቋመ መደብር ነበር። የንብረቱ ስፋት በጥግግት 0.48 ኤከር የሆነ እና ለ ማህበረሰባዊ ንግድ ጥቅም ላይ እንዲውል ተብሎ የተከለለ ነው



የ Boathouse Inc Renton Skyway የጽዳት ቦታ የወፍ በረር እይታ

የKen Skyway Cleaners የደረቅ ጽዳት አገልግሎት በመስጠት ከ 1982 እስከ 2002 የሰራ ነው። በደረቅ ጽዳት ንግዱ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ መርዛማ ኬሚካሎች አፈርን እና የከርሰ ምድር ውሃን በክለዋል።

GG ይህንን አከባቢ መልሶ ለመገንባት የሚያስችለውን እንደ Skyway Towncenter project (Project) የግዢ እና ሽያጭ ስምምነት በመፈጸም ላይ ይገኛል። ይህ ብዙ አገልግሎት የሚሰጥ፣ ለብዙ ቤተሰቦች የሚሆን የመኖሪያ ፕሮጀክት የሚከተሉት ነገሮች ይኖሩታል፡

- በአማካይ 250 አጠቃላይ ክፍሎች
- ቢያንስ 50 በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የኪራይ ክፍሎች (ከአጠቃላይ ክፍሎቹ 20%)
- 30,000 ጫማ ካሬ የሚሆን የ ንግድ፣ የቢሮ እና የማህበረሰብ ቦታ

እነዚህ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ ክፍሎች ከ area median income (AMI) (የመካከለኛ ኑሮ ያላቸው ሰዎች ገቢ) 60%-80% በሆነ የኪራይ ዋጋ የሚቀርቡ ይሆናል። AMI በየዓመቱ በ ለእያንዳንዱ ካውንቲ በ Department of Housing and Urban Development የሚሰላ ነው። ለዚህ ቦታ የሚሆኑ የንድፍ ሃሳቦች ከ ማህበረሰቡ በሚገኝ አሰተያየት እና ከ አከባቢያዊ አርቲስቶች የሚገኙ የጥበብ ስራዎች መካከል የሚመረጡ ይሆናል። በዚህ ንብረት መልሶ ማልማት ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች ወይም አስተያየቶች ካሉዎት፣ እባክዎን አስተያየትዎን እዚህ ላይ ይስጡ። https://bit.ly/SkywayTowncenter

## ብክለት

ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ እና በአጎራባቹ ቦታ ላይ የአሟሚ ብክለት የደረሰበት የከርሰ ምድር ውሃ እንዳለ ተረጋግጧል። የብክለቱ መጠን በሚደረግ ምርምራ የሚረጋገጥ ይሆናል። ለ Skyway የውሃ ዲስትሪክት (በአማካይ 9,890 ተጠቃሚዎች) እና የ Renton ከተማ (በአማካይ 62,100 ተጠቃሚዎች) አገልግሎት የሚሰጡ የከተማ አስተዳደሩ የውሃ ጉድጓዶች፣ ክግንባታ ቦታው በ 2 ማይል ርቀት ላይ የሚገኙ ናቸው።

የተካሄደው ምርመራ የሚከተሉት ብክለቶች በአፈር ላይ እና በከርሰ ምድር ውሃ ላይ እንዳሉ አረጋግጧል፡

- Tetrachloroethene (PCE)
- trichloroethene (TCE)
- cis-1,2-dichloroethene (DCE)
- vinyl chloride (VC)

ሁሉም እነዚህ ብክለቶች ከግዛቲቱ የጽዳት ህግ፣ Model Toxics Control Act(MTCA[1]) (የመርዛማ ንጥረ ነገሮች ቁጥጥር ሞዴል

[1] www.ecology.wa.gov/mtca

አዋጅ) በላይ በሆነ መጠን የተገኙ ናቸው። MTCA እነዚህ በካይ ንጥረ ነገሮች እንዲጸዱ ያዛል።

## ለምንድን ነው ይህ ቦታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው

ከፊሉ የዚህ ቦታ የጽዳት ሂደት እውን ሊሆን የቻለው በ Ecology Affordable Housing Cleanup Grants(በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የመኖሪያ ቤቶች የጽዳታ ገንዘብ ድጋፍ) በኩል በተደረገ የገንዘብ ድጋፍ ነው።[2].

በመላው የ Washington ግዛት ውስጥ ከባድ የሆነ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎት አለ። ብክለት ወይ ብክለት አለ የሚለው ጥርጣሬ የቤት ልማት ዋጋን ከፍ የሚያደርግ ነው። ይህ ከፍተኛ የሆነ ዋጋ አልሚዎች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ ቤቶች እንዲገነቡ የሚያስችል ማበረታቻ አናሳ እንዲሆን የሚያደርግ ነው።

ከተለመዱት የመልሶ ማልማት አደጋዎች በተጨማሪ፣ የተበከሉ ቦታዎችን ማጽዳት ውስብስብ እና አደጋዎችን ሊያስከትል የሚችል ሂደት ነው። አንድን ቦታ ለማጽዳት የሚያስፈልግ ወጪ እና የሚያስፈልገው ግዜ አብዛኛውን ግዜ ተገቢ የሆነ ግንዘቤ የተያዘበት አይደለም፡ በውጤቱም፣ ብዙ ቦታዎች ለ ዓመታት ወይም ምናልባትም ለ አስርት ዓመታት ባዶ ወይም ከደረጃ በታች የሆነ ጥቅም እየሰጡ ናቸው። በተመጣጣኝ ዋጋ ለሚቀርቡ የመኖሪያ ቤቶች የሚካሄዱ የጽዳት ስራዎችን መደገፍ፣ የጽዳት ስራው እንዲጠናቀቅ እና የማህበረሰቡ ጤና እና አከባቢው እንዲጠበቅ የሚያደርግ ነው።

በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የመኖሪያ ቤት ጽዳት የገንዘብ ድጋፍ መርሃ ግብር (Ecology Affordable Housing Cleanup Grant Program, AHCGP) ን ያበለጸገው፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ መኖሪያ ቤት ልማት ላይ የሚካሄዱ የ አከባቢ ጽዳቶች ደረጃቸው ከፍ እንዲል ለማገዝ ነው። እነዚህ የገንዘብ ድጋፎች እንደ ዕቅድ ማውጣት፣ ምርመራ ማካሄድ እና የተበከሉ ቦታዎችን ለማጽዳት የሚያስችሉ ቴክኒካዊ ስራዎችን ለመሰራት የሚውል የማሻሻያ ስራዎች ዋጋ ለመሸፈን የሚችሉ ናቸው። የ AHCGP ዋና ዓላማ በተበከሉ አከባቢዎች ላይ የሚኖር የጽዳት ስራ እና ወደ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ ቤቶች የሚወስድ የመልሶ ማልማት ስራን ለማፋጠን እና የጽዳት ዋጋዎችን ለመቀነስ ነው።

## ከዚህ ቀጥሎ ምንድን ነው የሚሆነው?

Ecology ሁሉንም የሚሰጡ አስተያየቶች ተመልክቶ በአስተያየቶቹ መሰረትም ሰነዶቹን ሊያሻሽል ይችላል። ከዛ በኋላ፣ PPCD እና የህዝባዊ ተሳትፎ ዕቅድ (Public Participation Plan) ዝግጅት በማጠናቀቅ፣ የጽዳት ስራው መደበኛ በሆነ መንገድ ይጀመራል። የማሻሻያ ምርመራ እና የአዋጭነት ጥናት ይጠናቀቃሉ። ከ ማሻሻይ ምርመራው እና ከ አዋጭነት ጥናቱ የሚገኙ ውጤቶች ወደ የጽዳት እርምጃ ዕቅድ የሚመሩ ይሆናል። የማሻሻያ ምርመራ እና የአዋጭነት ጥናት ረቂቆች እንደዚሁም Cleanup Action Plan (የጽዳት እርምጃ ዕቅድ) ለህዝባዊ ግምገማ እና አስተያየት ይቀርባሉ። (ከስር ያለውን የግራፊክ ስእል ይመልከቱ።)

## የ Washington መደበኛ የጽዳት ሂደት




[2] https://ecology.wa.gov/Spills-Cleanup/Contamination-cleanup/Brownfields/Affordable-housing

Toxics Cleanup Program
PO Box 330316
Shoreline, WA 98133

## የ አስተያየቶች ግብዣ - Boathouse Inc Renton Skyway የጽዳት ቦታ



የ Boathouse Inc Renton Skyway የጽዳት ቦታ የወፍ በረር

### የህዝባዊ አስተያየት ጊዜ

**ጁላይ 18 – ኦገስት 16, 2022**

https://bit.ly/Ecology-Boathouse

### የኦንላይን ህዝባዊ ውይይት

**ረቡዕ, ኦገስት 3, 2022**

- **6:30 – 7:00 p.m.** ገለጻ
- **7:00 – 7:30 p.m.** የጥያቄ እና መልስ መርሃ ግብር

የምዝገባ እና የአባልነት ዝርዝሮችን ለማግኘትhttps//bit.ly/Ecology-Boathouseን ይጎብኙ።

የአቅርቦት ጥያቄዎች፡ ከእይታ ጋር የተያያዘ ችግር ላለባቸው ሰዎች የሚሆኑ የቅጾች ወይም ሰነዶች ፎርማቶችን ጨምሮ ሌሎች የአቅርቦት ጥያቄዎችን ለ ADA ለማቅረብ ለ Ecology በ 206-594-0000 ተጠቅመው ይደውሉ ወይም https://ecology.wa.gov/accessibility ይጎብኙ። የመስማት ችግር ያለባቸው ሰዎች ወደ Washington የ Relay አገልግሎት ለማግኘት 711 ላይ ይደውሉ። ከንግግር ጋር የተያያዘ ችግር ያለባቸው ሰዎች ወደ (TTY, teletypewriter) 877-833-6341 ላይ መደውል ይችላሉ።